Minnesota Department of Health • የባዮቴሮሪዝም መረጃ 10/8/2005

# ቦትዩሊ.ዝም

## ቦትዩሊ.ዝም ምንድን ነው?

ቦትዩሊ.ዝም በመርዝ ሰበብ የሚከሰትና እስከ ሞት የሚያደርስ አደገኛ በሽታ ነው። ቦትዩሊ.ን ቶክሲ.ን ተብሎ የሚጠራው መርዝ በአንድ ዓይነት ረቂቅ ሕዋስ (bacteria) አማካኝነት የሚፈጠር ሲሆን በሳይንስ ዓለም ውስጥ ከሚ.ታወቁ መርዞች ሁሉ አደገኛው ነው።



*በቦትዩሊ.ዝም ረቂቃን ነፍሳት የተበከሉ እቤት ውስጥ የታሸጉ የቆርቆሮ ምግቦች*

ቦትዩሊ.ዝም በሕክምና ዓለም ውስጥ ከባድ ጥንቃቄ የሚያስፈልገው በሽታ ከመሆኑ በተጨማሪ በአደገኝነቱ የሚ.ታወቅ ነው። ይህም በሽታ የመተንፈሻ አካላት ጡንቻዎችን በማድከምና ሽባ በማድረግ የሰውን ልጅ ሕይወት ሊያሳልፍ ይችላል፤ ሆኖም ግን በአለፉት 50 ዓመታት ውስጥ ለበሽታው የሚሰጠው ሕክምና እየተሻሻለ በመምጣቱ በዚሁ በሽታ የተያዙ ሰዎች የመሞት ዕድላቸው ከ 50 በመቶ ወደ 8 በመቶ ቀንሷል።

በአሜሪካን አገር ውስጥ በአማካይ በዓመት 110 የቦትዩሊ.ዝም ታማሚዎች ይገኛሉ።

## ቦትዩሊ.ዝም የሚይዘው እንዴት ነው?

በተፈጥሮ ሰው ቦትዩሊ.ዝም ሊ.ይዘው የሚችለው በሶስት የተለያዩ መንገዶች ነው፦

- በመርዙ የተበከለ ምግብ በመብላት
- ረቂቃን ነፍሳቱ የበከሉት ቁስል በሚፈጥረው መርዝ
- አንድ ሕፃን ልጅ የረቂቃን ነፍሳቱን "ስፖር" - ማለትም ረቂቃን ነፍሳቱ ማደግና መራባት ሲያቅታቸው የሚይዙት ጠንካራ የቅርፊት መልክ - የያዘ ምግብ ሲበላ ወይም ሲጠጣ።

ከዚህም የተነሳ ሆን ተብሎ ምግብ ውስጥ በመጨመር እና ሰዎች ወደ ውስጥ በሚስቡት አየር ላይ በመልቀቅ የቦትዩሊ.ዝምን መርዝ እንደ ጦር መሣሪያ መጠቀም ይቻላል ተብሎ ይታመናል።

## ምልክቶቹ ምንድን ናቸው?

ሰው የሚ.ይዘው መንገድ ይለያይ እንጂ የቦትዩሊ.ዝም ምልክቶች ሁሉ አንድ ዓይነት ናቸው። እነሱም ዐይን ሁሉን ነገር ሁለት አድርጎ ሲያይ፣ ብዥ ሲ.ል፣ የዐይን ሽፋን መውደቅ ሲ.ጀምር፣ ሲ.ናገሩ መንተባተብ ሲ.ጀምር፣ ለመዋጥ ሲያስቸግር፣ አፍ ሲደርቅና የጡንቻ ድካም ናቸው። ቦትዩሊ.ዝም ያለባቸው ሕፃናት ዝልፍልፍ ይላሉ፣ ምግብ በደንብ አይመገቡም፣ ድርቀት ይይዛቸዋል እንዲሁም ደካማ ለቅሶና የጡንቻ ድክመት ይታይባቸዋል። እነዚህ ሁሉ ምልክቶች በመርዙ ምክንያት የሚመጣውን የጡንቻ ሽባነት የሚያሳዩ ናቸው። ሕክምና ካላገኙ ቦትዩሊ.ዝም ያለባቸው ሰዎች የክንድ፣ የእግር፣ የወገብ ጡንቻዎችና ለመተንፈስ የሚጠቀሙባቸውን ጡንቻዎች ሽባነት ሊ.ደርስባቸው ይችላል።

ቦትዩሊ.ዝም በተበከለ ምግብ ምክንያት ከተከሰተ ምልክቶቹ ከ18 እስከ 30 ሰዓታት ባለው ጊዜ ውስጥ ይታያሉ። ሆኖም ከስድስት ሰዓት በኋላ ወይም ከ10 ቀን በኋላ ሊ.ጀምሩ ይችላሉ።

## ቦትዩሊ.ዝም ከሌላ ሰው ሊ.ይዝ ይችላል?

አይችልም። ቦትዩሊ.ዝም የመርዝ ዓይነት ነው። ሕይወት ባለው ሕዋሳት ምክንያት የሚፈጠር አይደለም - ከሰው ወደ ሰውም ሊ.ተላለፍ አይችልም።

## ቦትዩሊ.ዝም ሊ.ታከም ይችላል?

ለማንኛውም ዓይነት ቦትዩሊ.ዝም መሠረታዊ ሕክምናው ሆስፒ.ታል ውስጥ የሚደረግ ጥንቅቄ ነው። ይህም በሽተኛው ለመተንፈስ የሚረዳው መንገዶችን ሊ.ያጠቃልል ይችላል። በሽታው በጊዜ ከታወቀ መርዙ የሚያስከትለውን ሕመሞች ለማስቀረት መድሃኒቶች መውሰድ ይቻላል - እነዚህ መድሃኒቶች ግን ሕፃናቶችን ለማከም መጠቀም አይቻልም። የተበከለውን ምግብ ከበሽተኛው ሆድ ዕቃ ማስወደግ ይቻላል። ሰዎች ቦትዩሊ.ዝም ከቁስል

MINNESOTA MDH DEPARTMENT OF HEALTH
Communications Office
625 North Robert Street/Box 64975
St. Paul, MN 55164-0975
(651) 201-4989
www.health.state.mn.us

ሲይዛቸው መርዙ የመጣበት ምንጭ በቀዶ ጥገና ተቆርጦ ሊወጣ ይችላል።

በሽታው አስጊ ከሆነ ከቦትዩሊዝም ለመዳን ብዙ ሳምንታት ወይም ወራት ሊፈጅ ይችላል። በሽታው የሚያስከትላቸው ነገሮች - ማለትም ድካምና የትንፋሽ ማጠር ሊሆኑ ይችላሉ - እስከ ብዙ ዓመታት ሊቆዩ ይችላሉ።

## ቦትዩሊዝምን መከላከል ይቻላል?

አጠቃላይ ሕዝቡን ከቦትዩሊዝም ለመከላከል የሚሰጥ ክትባት የለም። የቤተ ሙከራ ሠራተኞችንና የጦር ሰራዊቶችን ለመከላከል የሚጠቀሙበት የሙከራ ክትባት አለ። ከምግብ የሚመጣ ቦትዩሊዝምን ለመከላከል ምግብን በጥንቃቄ መያዝ አስፈላጊ ነው - በተለይ እቤት የሚታሸጉ የቆርቆሮ ምግቦች አሳሳቢ ሊሆኑ ይችላሉ። ከ12 ወር ዕድሜ በታች ያላቸው ሕፃናቶች ማር መመገብ የለባቸውም ምክንያቱም አንዳንድ ጊዜ ማር የቦትዩሊዝም "ስፖሮችን" ሊይዝ ይችላል።

## ቦትዩሊዝም የሽብር መፍጠሪያ መሣሪያ ሊሆን ይችላል ተብሎ የሚታመነው ለምንድነው?

በቦትዩሊዝም ረቂቃን ነፍሳት የሚፈጠረው መርዝ በጣም ኃይለኛና የሚገድል ነው። መርዙን ለመሥራትና ለማጓጓዝም ቀላል ነው። ቦትዩሊዝም የሚይዛቸው ሰዎች ረጅምና በኃይለኛ ጥንቃቄ የሚደረግ ሕክምና ያስፈልጋቸዋል። ቦትዩሊዝም በሰፊው ቢራባ ከባድ የዕለታዊ እንቅስቃሴ መዛባት ሊፈጥር ይችላል።

ቦትዩሊዝምን እንደ ጦር መሣሪያ ለመጠቀም ሙከራዎች መደረግ የተጀመረው ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጀምሮ ነው። ከ 1970 ዓ.ም. ጀምሮ አንዳንድ አገሮች ቦትዩሊዝምን እንደ ጦር መሣሪያ የመጠቀሚያ መንገድ እያገኙ ነው ወይም አግኝተዋል። ጃፓናዊ የሃይማኖት አምልኮ ተከታዮች ከ1990 ዓ.ም. እስከ 1995 ዓ.ሞ ባለው ጊዜ ውስጥ ቢያንስ ሶስት ጊዜ በቶኪዮ አካባቢ የቦትዩሊዝም መርዝን አየር ውስጥ ለመልቀቅ ሞክረዋል።

## ቦትዩሊዝም ያለብኝ ከመሰለኝ ምን ማድረግ አለብኝ?

ማንኛውም ዓይነት የቦትዩሊዝም ምልክቶች ካሉብዎት ዶክተርዎ ጋር በአስቸኳይ ይሂዱ። ቦትዩሊዝምን ወይም ማንኛውንም ዓይነት ሌላ በሽታን እንደ ጦር መሣሪያ ለመጠቀም የሚደረግ እንቅስቃሴ በሠፈርዎ ውስጥ ካዩ በአካባቢዎ ለሚገኘው የሕግ ማስከበሪያ ድርጅት በአስቸኳይ ያሳውቁ።